ማነው ዶክተር በዛብህን የመኢአድ መሪ እንዳልሆነ እየታወቀ ፡ ወደ አሜሪካን ያመጣው?
ይላል የኢትዮጵያ ሕዝብ በአገር ቤት እና በውጪ የሚገኘው።




## ካባ ቢቀያየር ማንነትን አቀይርም

ሰላም ወገኖቼ ጠላትክን ለማጥቃት ስትነሳ ከጀርባክ ያለውን ጠንቅቀን ማወቃችን ጥቅም ብቻ ሳይሆን አዋቂነትም ነው።

በቅርቡ ካባውን ቀይሮ ብቅ ስላለው ስለ ዶክተር አክሎግ ቢራራ የእባብ መርዙን በወገኖቼ ላይ ሊተፋ መሞከሩ ብዙሀኑን አስገርሞል፡

እኔም ቪዲዮውን ከማቅረቤ በፊት እንደምታውቁት ለአማራ ተቆርቋሪ መስሎ አማራውን እየሰለለ ለወያኔ እያቀረበ አማራውን እያስመታ ያለ መናጢ ሰው መሆኑን ብዙዎቹ ነግረውኛል።

በቅርቡ የመኢአድ መሪ አቶ ማሙሸት አማረ በወያኔ እስር ቤት እየተሰቃየ  እያለ !
ዶክተር  አክሎግ በወያኔ የተሾመውን  ዶክተር  በማስመጣት መኢአድን ለማጥፋት ካባቱ ከወያኔ የተሰጠውን ጭካኔ ተልኮውን ሲሰራ ተመልክተናል።

ወገኖቼ በቅርብ እየሰራ ያለው ከአቶ አረጋዊ በርሄ ጋር ሲሆን ይህ ግለሰብ የአማራን ህዝብ የጨፈጨፈ በኢትዮጲያ ህዝብ ተፈላጊ ከሆነው ጋር በቅርብ ሆኖ በሚስጥር የሚሰራ የአማራ ህዝብ ጠላት ሆኖ ሳለ የቀሩትን ደግሞ ጀግና የአማራ ልጆችን ለማስመታት የታሉ እያለ ሲያስመስል ተመልክቼ ስላሳዘነኝና ወገኔ ጠንቀቅ እንድትሉት ነው።

“የአማራ ልሂቃን የአማራ ሕዝብ እየተገደለ እያዩ እና የአማራን መደራጀት እየገፉ እስከመች ይኖራሉ? ዶ/ር አክሎግ ቢራራ

ዶ/ር አክሎግ ቢራራ በአማራ እና በሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ እየደርሰ ያለው ግድያና ጭፍጨፋ እንቅልፍ ከነሳቸው ኢትዮጵያውያን አንዱ ናቸው።

ዶ/ር አክሎግ ብራራ ከሕብር ራዲዮ ጋር ባደረጉት ቃለመጠየቅ የአማራ ልሂቃን እስከመቼ የአማራን መደራጀት እየገፉ ይኖራሉ በማለት ለአማራ ሊቅሃን ጥያቄ ያቀርባሉ። መሉ ቃለ መጠየቁን ከዚህ በታች ያዳምጡ።”
https://youtu.be/u9G_4LKEMMQ

አታፍርም ይህን ለማለት መነሳትህ በራሱ ይገርማል ያው ስራህን እየሰራህ እንደሆነ እናውቃለን ወያኔም ይወድቃል መንግስት ይቀየራል ህዝብን መካድ በህዝብ ላይ ሸምቅ መፈፀም ግን እስከ ትውልድ ዋጋ ያስከፍላል።

ወገኖቼ አንዳንዴ ይህ ግለሰብ ለምን ከላይ ያሳየሁትን ኢንተርቪው ለማድረግ ምን አነሳሳው ?
የሚለውን ሳስብ ድንገት ትዝ ያለኝ ለዶክተር አክሎግ ግን ረጅም ዝግጅት አርጎበት አስቦት ያደረገው መሆኑ ሲገባኝ አናደደኝ ለምን የሚለውን ለማወቅ ይህን ከዚህ በታች ያለውን ያዳምጡ።”
http://www.ethiopatriots.com/Interview/Yeharerwork-Gashaw-Ethiopia-Andnet-Radio-Stockholm-Sweden-20180121.mp3

ዶክተር አክሎግ  ለዚህ መልስ ለመስጠት ነው  እንግዲህ ከአባሪዎቹ ጋር ሆኖ ያደባውን ነው ያወጣው ስለዝህ ይህን እኛን መሳይ ካባውን እየቀያየረ የቀረበንን መጠንቀቅ እንዳለብን አውቀነው የመኢአድ መሪዎችን አሳስረህ  አሁን ደግሞ ድምጥማጡን ለማጥፋት አስመሳይ በመሆን አትደከም እንበለው ትግሉ ከዚህም በላይ የመረረ ነው።

ድል ለመኢአድ
ድል ለኢትዮጲያ ህዝብ
አስመሳይ ሰላዮችን በጋራ እንታገላቸው !

https://ecadforum.com/2014/01/06/global-alliance-donates-funds-to-international-organization-for-migration-iom/

ከዚህ በታች የተለያየ ኢትዮጵያውያን ስለ አክሎግ እና ግብረ አበሮቹ ካስከመጡት መሃል
በሸንቁጥ አየለ የተጻፈውን ተመልከቱት።

“ሸንጎ የሚባለዉ ስብስብ በመኢአድ ጀግኖች ደም ጭቃ ሲያቦካ:-
እነ ማሙሸት አማረ በስር ቤት መከራ እየተቀበሉ አረጋዊ በርሄ ዶ/ር በዛብህን ይዞ ከስብሃት ነጋ ጋር
ስላንተ ይደራደርልሃል !

ሸንቁጥ አየለ

አረጋዊ በርሄ የሚባል ተንኮለኛ ሸንጎ የሚባል ስብስብ ይመራል::አረጋዊ በርሄ ልክ የኢትዮጵያ ህዝብ
ድምጹን ለቅንጅት ሰጥቶ ቅንጅት በመላ አገረቱ እንዳሸነፈ ሲሰማ አንድ መግለጫ ሰጠ::"
ቅንጅት የኢትዮጵያን ህዝብ የመምራት የሞራል ብቃት የለዉም:: ምክንያቱም ቅንጅቱ
የነፍጠኞች ስብስብ ነዉና" ሲል።

ወዲያዉ መለስ ዜናዊ በቅንጅቱ ላይ የማያዳግም እርምጃ ለመዉሰድ የአረጋዊ በርሄን መግለጫ በመከተ
ል መግለጫ ሰጠ::አቦይ ስብሃት የተባለዉ እባብም "ከአማራ ነፍጠኞች ጋር ድርድር እና የስልጣን ክፍ
ፍል አያስፈልግም::ቅንጅትን ፈጽሞ መደምሰስ ያስፈልጋል" ሲል ትንታኔ ሰጠ።

አረጋዊ በርሄ: መለስ ዜናዊ እና አቦይ ስብሃት አቋማቸዉ አንድ ነበር::ሰላማዊ የሆነዉን የኢትዮጵያ
ህዝብ ምርጫ መደምሰስ እና በአማራ ህዝብ ላይ የጠላትነት ቂም ማራመድ።

ዛሬም አረጋዊ በርሄ አክራሪ የኢትዮጵያዊነት አቋም አላቸዉ የሚላቸዉ እነ ማሙሸት አማረን
ከኢትዮጵያ ፖለቲካ ለማዉጣት እየሰራ ነዉ።

ገንዘብ አቋም ይገዛል::ግለሰቦችን ከእነ ስሜታቸዉ ጭምር:: ሆኖም አለም ላይ ለህሊናቸዉ እና ለአቋማ
ቸዉ ኖረዉ የሚሞቱ ጥቂት ሃያላን ነብሶች አሉ::ከነዚያ ሀያላን ነብሶች መሃከል ጀግናዉ ማሙሸት አማ
ረ የሚመራው የመላዉ ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት/መኢአድ/ አናብስት ተጠቃሽ ናቸዉ።
እነዚህ ስብስቦች ሲያስተዉሏቸዉ ኮሳሳ ይመስላሉ::ግን እጅግ ጽኑአን እና ሀያላን ናቸዉ::ስብስባቸዉ
ከሰሜን ኢትዮጵያ እስከ ደቡብ ኢትዮጵያ ነዉ።

ስለ ኢትዮጵያ ሲያወሩ ዉለዉ ቢያድሩ አይሰለቻቸዉም::የኢትዮጵያን ትንሳኤ እና መዳን ሀያ ስድስት
አመታት ሙሉ ሲያስሡ ኖረዋል::አሁንም አልታከታቸዉም::እየታሰሩም ስለ ኢትዮጵያ ይቃትታሉ::
አንዳንዴ ይገርማል:: ኢትዮጵያ ዉስጥ ባህል የሆነዉ የአየር ባየር ንግድ ነዉ::ሁሉንም ነገር መሸጥ እና
መግዛት እንደ ጀግንነት ይቆጠራል::የዘማ ፖለቲካ ማለት ይሄ ነዉ::በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎችን
ሲያሳርድ የነበረ ሰዉዬን ተቃዋሚ ነኝ ያለ እንደሆነ ደጋፊ እና አብሮት የሚያናፋ አያጣም፣
ትናትን አይታሰብም።

የአየር ባየር ንግድ ወሳኝ ነዉ በሚል ስንኩል ባህል አገሪቱ ተወራለች:: በዚህም ቀመር መሰረት ምርጫ
ቦርድ ሲጠራቸዉ እና ሲያዛቸዉ የሚስማሙትን ጥቂት ሰዎች ከመኢአድ ሰዎች

መርጦ በመኢአድ ላይ ሾሟቸዋል::እነ ዶክተር በዛብህ: እነ አበባዉ መሃሪ: እነ ሙሉጌታ ለዚህ አላማ በ ወያኔ ተመርጠዉ የዘማ ፖለቲካቸዉን ተያይዘዉታል ገንዘብ ይሰጣቸዋል።

እነሱ የህዝቡን ፖለቲካ ለወያኔ ይሸጡታል::ከህዝቡ መሃል የሚታለል እና አብሯቸዉ የሚቆም አያጡም::

ወያኔ 122(መቶ ሃያ ሁለት) የመኢአድ አመራሮችን አስሯቸዋል::ማሰር ብቻ አይደለም እያሰቃያቸዉ ነዉ::የናዚ ስቃይ::ያሰራቸዉ ደግሞ ህዝባዊዉን ተጋድሎ መርታችኋል በሚል ነዉ:: ኢሳት ሳይቀር

በዉጭ ሀገር ያሉ ሚዲያዎችሲያናፉበት የነበረዉ ተጋድሎ ይሄ ተጋድሎ ነዉ::የአማራ ተጋድሎን እነመ ራለንብለዉ ብቅ ብቅ ያሉ ሰዎች ሁሉ ሲያናፉበት የነበረዉ ተጋድሎ ይሄ ነዉ::ግን ስለ እነዚህ ስለታሰሩ 122የመኢአድ አመራሮች አንድም ትንፍስ የሚልየለም:: የገማ ፖለቲካ እና የገማ ማህበረሰሰባዊ እሴት ይልሃል ይሄ ነዉ:: ሁሉም የሚሮጠዉ እኔ ተጋድሎዉን መራሁት ለማለት ነዉ እንጅ ስለሚጋደሉት እና ስለሚዋደቁት ሰዎች ግድም አይሰጠዉም።

አሁን በዉጭ ሃገር ያሉ ሚዲያዎች እና ባንዳዎች ግን እነበዛብህ እና እነ አረጋዊ በርሄን መርጠዋል። አረጋዊ በርሄ በመኢአድ ጀግኖች ድርጅት ላይ እንዲያናፋ ተፈቅዶለታል::ህሊናቢሱ የዉጭ ሀገር ሚዲያ እዉነት መመርመር አያዉቅም።

ያገኘዉን ሁሉም መትፋት ልማዱ ነዉ:: መቻቻል ይልሃል::ግን መቻቻል እና ጠላትነትን እንኳን አያዉቅም:: ብልታቸዉ የሚቀተቀጠዉ እና መከራ የሚቀበሉት አንዴ ዘራቸዉ እየተቆጠረ ሌላ ጊዜ ድርጅታቸዉ እየተጠራ ነዉ።

ዘራቸዉን ከሚጠላዉ እና ድርጅታቸዉን ሊያጠፋ የሚያደባዉ አረጋዊ በርሄ ግን ዛሬ በመኢአድ ወያኔ ከሰየመቻቸዉ ሰንኮፎች እነበዛብህ ጋር በመሆን ስቃይ ይሳለቃል።

የመኢአድ ምክትል ፕሬዘዳንት አቶ ዘመነ ምህረት በስደት በሰዉ አገር በየቀኑ በሚደርሱበት በርካታ የወያኔ ስለላ: የግድያ ሙከራ እና ብዙ ስቃዮች እሳት ላይ ተጥዶ ትግሉን አላቆመም::ይሄ ሁሉ የሚደርስበት ከህዝቡ ተጋድሎ ጋርአብሮ ስለቆመ እና እዉነተኞቹ የመኢአድ አናብስት የሚያራምዱትን ትግል ስለሚመራ ነዉ::እነ ኢሳት ይሄን ጀግና ማቅረብም ሆነ መጠዬቅ አይፈልጉም::ኢሳት የሚመርጠዉ ማንን ነዉ? የወያኔ ተላላኪዉን ዶክተር በዛብህን ነዉ።
ኢሳት የሚመርጠዉ እነ አረጋዊ በርሄን ነዉ። ለምን? እኮ ለምን?

በታላቅ ህዝባዊ እንቅስቃሴአቸዉን እስር ቤት የተወረወሩትን ህዝባዊ ታጋዮች ለምን እስር ቤት ገቡ ብሎ የሚጠይቅ ሀይል የለም::ሀገር በሆያሆዬ : እና ለዉጥ በባንዳ አሰራራ ይመጣል ብሎ ያመነዉ ወገን አሁን በተዘዋዋሪ ከወያኔ ጋር ተባብሮ እየሰራ ነዉ:: አረጋዊ በርሄ ለዉጥ ያመጣልኛል ብለህ የምታስብ

ካለህ መንገዱን ጨርቅ ያድርግልህ።
ፕሮፌሰር መስፍን እንዳሉት አልምጥ ህዝብ የራሱን ሀገር በባለቤትነት ከምቆጣጠር እና እዉነተኛ ለዉጥ እንዲመጣ ከመስራት ይልቅ ለዉጥን ከባንዶች እና ከዘማ ፖለቲካ አራማጆች

አንጋጦ ከጠበቀ ትርፉ እንዘጭ እንተፍ ነዉ።

እነ አረጋዊ በርሄ የሚመሩት ሸንጎም አሁን እነ ዶ/ር በዛብህን በመያዝ በጋራ እንሰራለን እያለ ነዉ:: ሸንጎ እና እነ ዶ/ር በዛብህም ስለ ሽግግር መንግስት ከወያኔ ጋር እየመከሩ መሆኑ ነዉ። አስቡት ወያኔ እነ ዶ/ር በዛብህን ሾሞ። አረጋዊ በርሄ ስዉር እና ገሃድ ወያኔ ነዉ።

እናም ወያኔዉ ሸንጎ እና ዋናዉ ወያኔ አብረዉ ይደራደራሉ ማለት ነዉ።
በዉጭ ሀገር ያሉ ባንዳ ሚዲያዎች ጉዳዉን ያራግባሉ።ሌላዉ ቀሮቶ ኢሳት ይሄን የባንዳዎች ቅንጅታዊ ስብስብ ዋጋ ሰጥቶ የነዚህ ሰዎች አብሮ መስራት ለዉጥ

እንደሚያመጣ በማስመሰል ህዝብ ያጃጅላል:: ጀግኖቹ ግን በእስር ቤት ይማቅቃሉ::የኢትዮጵያ ህዝብ ከእነ አረጋዊ በርሄ ለዉጥ ይመጣልናል ብሎ አንጋጦ እንዲጠብቅ ፕሮፖጋንዳ ይቀልጣል።

ኢሳት እና እነ አባይ ሚዲያ የምንሰራው የነጻ ሚዲያ ስራ ነዉ ስለዚህ ሁሉንም አማራጮች ማቅረብ

አለብን ካሉ እነ ዘመነ ምህረትን ለማቅረብ ለምን አልፈቀዱም? ለምን?

ለማንኛዉም ከዶ/ር በዛብህ እና ከአረጋዊ በርሄ ጋር የምትሞዳሞድ ሁሉ እራስህን መርምር::ባንዳ እና የዘማ ፖለቲካ ኢትዮጵያን አያድናትም ብቻ ሳይሆን እራስህንም ያጠፋሃል:: በዋናነት ለራስህ ደህንነት ስትል ከነ አረጋዊ በርሄ መረብ እራስህን አርቅ።

መደምደሚያዉ ግን አንድ ነዉ:: ድሉ የማን ነው? ሕዝብንስ ከሩብ ምዕተ አመታታ በላይ ማታለል ይቻላል? መልሱ ህዝብን ምዕተ አመታት ሙሉ ማታለል አይቻልም::ድሉ የህዝባዉያን ነዉ::የመኢአድ አናብስት ሀይላት የዘማ እና የባንዳ ፖለቲካን ይጸየፋሉ።

ኢትዮጵያም ፈጽሞ ነጻ እስክትሆን ትግሉን አያቆሙም።
አንዷት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ

የመኢአድ አናብስት ሀይላት ህልማቸዉ ናትና ይሄ እስኪሆን ስራዉ አይቆምም።